# ቤርያ

ቁ. 39

በየወሩ እየታተመ በወረቀት፣ በኢሜይል፣ በፌስቡክ እና በቴሌግራም በነጻ የሚሰራጭ መጽሄት

እነዚህም [የቤርያ ሰዎች] በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና፡- ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው እለት እለት መጻህፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ (ሐዋ 17፡ 11)፡፡

| | |
|---|---|
| አዘጋጅ - አበበ መንገሻ (ዶ/ር)<br>አድራሻ - ዲላ ከተማ<br>ስ.ቁ. – 0936669160 | ኢሜይል - abebe.meng@gmail.com<br>ፌስቡክ ገጽ - Berea teaching<br>ቴሌግራም https://t.me/bereamagazineethiopia |

# የበአላት አከባበር

# ክፍል 2

በቁጥር 38 ላይ መጽሀፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን የደነገጋቸውን በአላት፣ የበአላቱን መንፈሳዊ ትርጉም እና በአዲስ ኪዳን መጻህፍት ውስጥ ስለበአል የተሰጡ ሀሳቦችን ተመልክተናል፡፡ በዚህ እትም ደግሞ እኛ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ የሆኑ እና መንፈሳዊ ያልሆኑ በአላትን ስናከብር መከተል ያሉብንን መንገዶች እንመለከታለን፡፡

## ክርስቲያናዊ የበአል አከባበር ዘዴዎች

በአል የምናከብርባቸውን ዘዴዎች ለመወሰን እንዲያመቸን መጀመሪያ በዚህ ዘመን በመካከላቸው የምንኖርባቸው አለማውያን በአልን እንዴት እንደሚያከብሩ መመልከት ይጠቅመናል፡፡

<u>የአለማውያን በዓላት አላማዎች</u>

አለማውያን በአላትን ለሰባት አላማዎች ይጠቀማሉ፡፡ አንደኛ በአላት የሚሰየሙበት የተለያየ ምክንያት ቢኖርም አለማውያን ግን የሚጠቀሙባቸው 'አለማውያን' የሚለው ስማቸው እንደሚጠቁመው ከስማቸው ለሚመነጨው አለማዊ ባህሪያቸው ማስፈጸሚያነት እና ለርኩሰት ማከናወኛነት ነው፡፡ ለምሳሌ የፍቅረኛሞች በአል ተብሎ የሚከበረው የቫለንታይን (የፍቅረኞች) ቀን በተባለው ግብሩን የሚመለከት ስም በወጣለት በአል ዝሙት ይሰራሉ፤ ይዳራሉ፤ ይዘፍናሉ፤ ይጨፍራሉ፤ ከጋብቻ ውጭ ያለ የፍቅር ግንኙነትን እና ልቅ ወሲብን ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ተግባራትን በየአደባባዩ፣ በየመገናኛ ብዙሀኑ እና በየህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች ያደርጋሉ፡፡ የቫለንታይን ቀንን እንደምሳሌ እንጠቅስ እንጂ ሌሎቹንም የሀይማኖት እና የባህል በአላት የሚጠቀሚቸው ለእነዚሁ ተግባራት ነው፡፡ ስጋዊ ፍላጎታቸውን ለመተግበር በአላትን እንደሰበብና ጥሩ አጋጣሚ ይቆጥሯቸዋል፡፡

ሁለተኛ ለመብላትና ለመጠጣት ነው፡፡ በተለይ በአገራችን የአለማውያን በአላት በመብላትና በመጠጣት የተሞሉ ናቸው፡፡ ብዙዎቹም አለማውያን በበአላት ቀናት የሚበሉትና የሚጠጡት የምግብ እና የመጠጥ አይነት ከዚያ በፊት የማይበሉትና የማይጠጡት ስለሆነ ወይም መጠኑ ከወትሮው ስለሚበልጥ ለህመምና ለስካር ይዳረጋሉ፡፡ በርግጥ በልኩ የሆነ መብላትና መጠጣት ችግር ባይኖርበትም ተግባሩ ሰዋዊና ምድራዊ ብቻ መሆኑ ግን እሙን ነው (1ቆሮ 11፡17-21)፡፡

ሶስተኛ ባህልን እና ማንነትን ለማሳየት ወይም ለማስጠበቅ እና ከሌላው ልዩ ወይም ተቃራኒ መሆንን ለማንጸባረቅ ነው፡፡ በአሉን የባህላቸውና የማንነታቸው መገለጫ ወይም ከሌላው የተለዩ መሆናቸውን ማሳያ አድርገው ይወስዱታል፡፡ አንዳንዶቹም በዚህ ሰበብ ወደባእድ አምልኮ ጎራ ብለዋል፡፡ በአገራችን ባለፉት ሶስት አስርተ ዓመታት የብሄረሰብ ባህሎችን በማሳደግ ስም ብዙ ተረስተው የነበሩ የባእድ አምልኮ ይዘት ያላቸው በአላት ለምሳሌ ሞራ መግለጥ፣ የከብት ደም ማፍሰስ፣ ውሃ ዳርና ዛፍ ስር ጸሎት ማድረግ፣ ልክ እንደ አቴናውያን በደፈናው አምላክ ለተባለ ነገር ምስጋና ማቅረብ እና የመሳሰሉ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

አራተኛ መደሰት በሚል ሰበብ ትርጉም የሌለው የመጃጃል ቀን ለማሳለፍ ነው፡፡ አንዳንዱ ተግባር ከመጃጃልም አልፎ መጎዳዳትም ሊያመጣ ይችላል፡፡ ለምሳሌ አፕሪል ዘፉል አንድን ሰው የሚያስነቅፉትን ተግባራት አታልሎ በማስፈጸም ወይም ያልተፈጸመ ስሜት የሚነካ ነገርን እንደተፈጸመ አድርጎ በመንገር ስሜት ውስጥ በማስገባት፣ በማስደንገጥ እና በማስነወር መሳቂያ የሚደረግበት በአል ነው፡፡ የስፔን የበሬ ውጊያ ጨዋታ ደግሞ ብዙዎችን ለመጋጋጥ፣ ለስብራት እና ለቁስለት ብሎም ለሞት ይዳርጋል፡፡

አምስተኛ የሰውን ታሪክ ለማውሳት፣ የሰውን ማንነት ለማጉላት እና ለመኩራራት በአጠቃላይ ሰው መሆንን ለማግነን ነው፡፡ ለምሳሌ የልደት ቀን፣ የሙት አመት እና የጦርነት ድል በአሎች በሙሉ የሰውን ስም ደጋግሞ በመጥራት፣ ለሰው በማጨብጨብ እና ሰውን በመሸለም ተጀምረው የሚጨረሱ በአላት ናቸው፡፡ የልደት ቀን መልካም ልደት ወይም እንኳን ደስ ያለህ የሚባለው ለሰውየው ነው፡፡ የሙት አመት የሚከበረው የሰውየውን ስኬቶችና ስራዎች በመተረክ ነው፡፡ የጦርነት ድል በአል የሚከበረው በጦር ግንባሮች የተገኘውን ድል በማተት፣ ጀግኖቹን በዘፈን በማወደስ፣ የጠላትን መሸነፍ በማጉላት እና የሞተውን የጠላት ወታደር በመቁጠር ነው፡፡

ስድስተኛ ሀብትን ለማሳየት ወይም ቸር ለመባል ነው፡፡ አንዳንዶች በአልን ግብዣ አድርገው ጎረቤትና ዘመድን በማብላት ቸር ለመባል እና ሀብት እንዳላቸው ለማስመስከር ሌሎች ደግሞ ድሃን ሰብስቦ በመርዳት ቸር እና ጥሩ ሰው የሚል ስም ለማትረፍ እንደጥሩ አጋጣሚ ይቆጥሩታል፡፡

ሰባተኛ ስለመንፈሳዊ ነገር እውቀቱ የሌላቸው ነገር ግን ከሞት በኋላ ስላለው ህይወት የሚያሳስባቸው ሰዎች በበአል ወቅት ስጦታን በመስጠት፣ የተራበን በማብላት ጽድቅን መግዛት የሚችሉ ይመስላቸዋል፡፡

<u>ክርስቲያን መንፈሳዊ ያልሆነ በአልን እንዴት ያክብር?</u>

እኛ ክርስቲያንኖችም የማህበረሰብ አካል እንደመሆናችን መጠን ማህበራዊ እና ባህላዊ በአላትን ልናከብር እንችላለን፡፡ በተለይ በተለይ የመንግስት ወይም የህዝብ የሃላፊነት ቦታ ላይ ከተቀመጥን፣ ታዋቂ ከሆንንና በማህበረሰቡ ዘንድ በስፋት የሚከበሩ የድል፣ የነጻነት፣ የልደት እና የመሳሰሉ እና እኛም እንደማህበረሰብ አባልነታችን ማክበር አለማክራችን በሌሎቹ ዘንድ ትኩረት የሚሰጠው ከሆነ እንፈተናለን፡፡ እንዲሁም የሚከታተለን ባይኖርም እንኳን እንደዜግነታችን ወይም እንደማህበረሰብ አባልነታችን ከሌሎቹ ጋር የምንካፈለው ስሜት ስላለን አንዳንድ በአላት ላይ የመሳተፍ ፍላጎት ሊኖረን ይችላል፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደተጠቀሰው የአለማዊያኑን አከባበር መከተል የለብንም፡፡ በአላቱ የተፈጠሩበትን ምክንያቶች የሚመለከቱ ስርአቶች ውስጥ በመሳተፉም ሆነ ሌሎች ተጨማሪ በግል ውሳኔ የሚከናወኑ ተግባራትን በመፈጸሙ ረገድ የራሳችንን ውሳኔ ለማድረግ የሚከተሉትን ክርስትናችንን መሰረት ያደረጉ መመዘኛዎች መጠቀም አለብን፡፡

የመጀመሪያው ሚዛን ተግባሩ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ስነምግባር ጋር አለመቃረኑ ነው፡፡ ከሁሉ በፊት የግል ቅድስናችን እንዳይነካ እና ጌታን እንዳናሳዝን መጠንቀቅ አለብን፡፡ ማንኛውም የበአል ተግባር የተለመደ መንፈሳዊ መታወቂያችንን ወይም ባህሪያችንን ሊያስጥለን እና ሊያስለውጠን አይገባም፡፡ ለምሳሌ በአንድ ወቅት በየዩኒቨርሲቲዎቻችን የእብዶች ቀን ተብሎ ልክ እንደእብድ ሆኖ በመዋል የሚከበር በአል ነበር፡፡ አንድ ትሁት የነበረ ክርስቲያን ይህን በአል በማክበር ሰበብ ሌላ ጊዜ የሚያከብራቸውን ሰዎች ቢደፍር በበአል ስም የሚጠበቅበትን መጽሀፍ ቅዱሳዊ ስነምግባር እየጣሰ፣ መልካም ባህሪውን እየጣለ እና በሌሎች ዘንድ ራሱን እያስነወረ መሆኑን ማወቅ አለበት፡፡ "በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ" የሚባል ነገርም በክርስትና ቦታ የለውም፡፡ የሚያስቆጣ ስራ በገና በአልም ሆነ በሌላ ቀን አናደርግም፡፡ እንዲሁም አንዲት ሴት ማርች ስምንትን (የሴቶች ቀንን) ስታከብር መጽሀፍ ቅዱሳዊው የባልና የሚስት ግንኙነት ቅድሚያ እንደሚሰጠው ሳትዘነጋ መሆን አለበት፡፡ ያን ብትጥስ መንፈሳዊነቷን እየጣለች መሆኑን ማወቅ አለባት፡፡ በመጨረሻም እኛ መንፈሳዊያን የሆንን ሰዎች ከቃሉ ጋር ተቃራኒ ከሆነ በባህል ስም የምናከናውነው ተግባር መኖር የለበትም፡፡ የክርስቲያን ዋና ባህል የእግዚአብር ቃል ስለሆነ ባህልን የምናስጠብቀው በቃሉ የታዘዝነውን ኑሮ እየኖርን ነው፡፡ ልዩ ናቸው ለመባልም በዓል አናከብርም፡፡

ሁለተኛው ሚዛን ወጥመድ ውስጥ እንዳንገባ አለማድረጉ ነው፡፡ አንዳንድ ስርአቶች እና ልማዶች ከላይ ከላይ ሲታዩ መልካም እና አስደሳች ወይም ተራ ልማዶች ቢመስሉም ከጀርባቸው ግን አላማ የሰነቁ አጋንንት ሊኖሩ ስለሚችሉ ከማድረጋችን በፊት ምንጫቸውንና አላማቸውን መመርምር ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ እነዚያን ተግባራት ስናደርግ ተግባራቱ ለአጋንንት እንደመሳሪያ ሊያገለግሉና ሰይጣን ህይወታችንን እንዲቆጣጠር ወይም

እንዲከታተለን መግቢያና መጋበዣ ሊሆኑት ይችላሉ፡፡ ሰይጣን በፊት ለፊት የሚያከብረው ሲያጣ ሰዎችን ሳያውቁ በእነዚህ መንገዶች ቀስ በቀስ አለማምዶ ወደህይወታቸቸው መግባት ይፈልጋል፡፡ ለምሳሌ እጣን ማጨስ፣ ጉዝጓዝ መጎዝጎዝ፣ የቡና ጭስ ማሽተት፣ በውሃ ዳርና በዛፍ ስር የተለያዩ ስረርአቶችን ማከናወን፣ ወዘተ የየራሳቸው ታሪክ ስላላቸው ከማድረጋችን በፊት ታሪካቸውን ማወቁ ይጠቅመናል፡፡ አንዳንድ መጽሀፍ ቅሳዊ ስም ያላቸው ነገር ግን ስማቸው ብቻ እንጂ ታሪካቸው፣ ትርጉማቸው እና አከባበራቸው መጽሀፍ ቅዱሳዊ መሰረት የሌለው፣ ለመዳን ያላቸው ጠቀሜታ አነስተኛ የሆነ ስለዚህም ሊከበሩ የማይገባቸው በአላት አሉ፡፡ ክርስቲያን እነዚህን መለየት እና መተው አለበት፡፡

ሶስተኛው ሚዛን ውስጣችን ለሌለ አላማ እንድንሰለፍ አለማድረጉ ነው፡፡ በአሉ የሚከበርበት ትርጉም ገብቶንና ከእኛ ማንነት ጋር ያለውን ዝምድና ተገንዝበን ብናደርግ ትርጉም የሌለው ነገር ከማድረግ ወይም የአንዳንድ ሰዎች አላማ ማስፈጸሚያ ከመሆን ይጠብቀናል፡፡ ለምሳሌ የቀለም ቀንን የሚያከብር ሰው ሰአሊ፣ ባለ ማተሚያ ቤት ወይም የቀለም ፋብሪካ ባለቤት ቢሆን ትርጉም ይሰጣል፡፡ እንዲሁም እኛ ኢትዮጵያውያን እንድናከብረው የሚያደርገን ከእኛ ባህልና ታሪክ ጋርም የተገናኘ ነገር የለውም፡፡ ነገር ግን በየዩኒቨርሲቲዎቻችን ተማሪዎቻችን ይህን ምንጩ የማይታወቅ በአል ለማክበር ጎንበስ ቀና ሲሉ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ለተማሪ ከዚህ ይልቅ የእውቀት ቀን ሰይሞ ማክበር የተሻለ ትርጉም ይሰጣል፡፡ እንዲሁም አንዳንድ ፖለቲካን፣ ህገ መንግስትን እና የሙያ ማህበራትን ተገን ያደረጉ በአላት የአንዳንድ ቡድኖች ርዕዮተ አለም አጃቢዎች፣ አስተዋዋቂዎች ወይም ስራ አስፈጻሚዎች ያደርገናል፡፡

አራተኛው ሚዛን የክርስትና አንድነታችንን አለመንካቱ እና የአካሉን አንድነት አለመጉዳቱ ነው (ኤፌ 4፡3)፡፡ በዘር ቢሆን በሙያ ወይም በዝንባሌ ቡድን የሚደረጉ በአላት በቡድኑ ውስጥ ሊካተቱ የማይችሉ ክርስቲያን ወገኖቻችን ጋር ያለንን ወንድማማችነት የሚጎዱ ወይም አደጋ ላይ የሚጥሉ ከሆነ ለኛ ተገቢ በአላት አይደሉም፡፡ የማንኛውም ክርስቲያን የመጀመሪያ ማንነት ክርስቲያንነት ነው፡፡ ዜግነት፣ የአንድ ብሄረሰብ አባልነት፣ የአንድ ዘር ተወላጅነት፣ የአንድ ሙያ ባለቤትነት፣ ጾታ ወይም የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ ተከታይነት ሁለተኛ ደረጃ ናቸው፡፡ እንዲሁም አንድ ሰው የመንግስት ለውጥ የተደረገበትን ብሄራዊ በአል ሲያከብር የወደቀውን መንግስት የሚወድ ወንድም ወይም እህት እንዳለው ሳይዘነጋና ያን ወንድሙን ወይም ያቺን እህቱን ለአዲሱ መንግስት በአል ሲል ሊያጣው ወይም ሊያጣት እንደማይገባ ጠንቅቆ መረዳት አለበት፡፡

አምስተኛው ሚዛን ክብር እና መልካምነት (Noblity, Virtue, Integrity) ያለበት መሆኑ ነው (ፊል 4፡8)፡፡ በበአል ስም የሚያስንቅ፣ የሚያጃጅል፣ የሚያዋርድ፣ የሚያሳፍር፣ ከተፈጥሮ ውጭ የሚያደርግ በአጠቃላይ ጥሩ ስሜት የማይፈጥር ተግባር ውስጥ መገኘት የለብንም፡፡ ለምሳሌ በበአል ወቅት ለክርስቲያን መጫወት ጥሩ ቢሆንም ጨዋታው የሚያጃጅል፣ ወደህጻንነት ደረጃ የሚያወርድ፣ በተራ ጊዜያት ለመገኘት የማንመርጥባቸው ቦታዎች እንድንገኝ የሚያስገድድ ከሆነ፣ ወዘተ አለመፈጸሙ ይመከራል፡፡ ክርስቲያን በመጃጃል እና በዋዛ ፈዛዛ የሚያሳልፈው ትርፍ ቀን የለውም፡፡

ስድስተኛ በአለማውያኑ ፊት ያለንን መንፈሳዊነት አለማቃለሉ እና አለማስነቀፉ ነው፡፡ አለማውያን ጋር ተደባልቀን በህብረት በምናከብረው በአል ውስጥ የምናከናውናቸው ነገሮች ትዝብት ውስጥ ሊጥሉን አይገባም፡፡ የምንሰብከውና የምንሰራው መስማማት አለባቸው፡፡ ድኛለሁ እያልን እየተናገርን ነገር ግን መዳናችን በተግባራችን የማይገለጥ ከሆነ አለማውያኑ ክርስትና የውሸት ሃይማኖት እንደሆነ ሊያስቡ ከዚህም የተነሳ እኛንም ሆነ ሌሎች ክርስቲያኖችን ሊሳደቡ ወይም ሊያንቋሽሹ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ አለማውያኑ መንካት ወይም ማድረግ የማንፈልጋቸው ነገሮች እንዳሉ ሊያውቁልን ይገባል፡፡ መንፈሳዊ ልዩነታችንን ጠብቀን ማክበር አለብን፡፡

ሰባተኛ ከአለማውያን ጋር ስጋዊ ዲሲፕሊናችንን በሚመለከት ባልተመቸ አኳኋን እንድንጠመድ የማያደርግ መሆኑ ነው (1ቆሮ 15፡33)፡፡ በበአሉ ሰበብ ከአለማውያን (መንፈሳዊ ነገርን ከማይረዱ ሰዎች) ጋር የጸሎት ጊዜያችንን፣ የስራ ዲሲፕሊናችንን፣ ለቤተሰብ ያለንን ትኩረት፣ ወዘተ የሚጎዱ እና ውስጣችንን የሚያሳዝኑ ግንኙነቶች ውስጥ እንዳንገባ መጠንቀቅ አለብን፡፡

<u>መንፈሳዊ በአል ከተከበረ እንዴት ይከበር?</u>

መንፈሳዊ በአላትን ስናከብር መከተል ያለብንን መንገዶች ለመለየት እግዚአብሄር በብሉይ ኪዳን ህዝቡ በአላትን እንዴት ማክበር እንዳለባቸው የሰጣቸውን መመሪያዎች መመልከት ያስፈልገናል፡፡

በብሉይ ኪዳን ሁሉም በአል ውስጥ የሚደረገው ስራ ከእግዚአብሄር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መስዋእቱ የሚቀርበው፣ የሚሰገደው እና የሚዘመረው ለእግዚአብሄር፤ የሚሰበከው እና የሚነገረው ስለእግዚአብሄር፣ የሚመሰገነው፣ የሚለመነው እና የሚወደሰው በሙሉ እግዚአብሄር ብቻ ነው፡፡ እነዚህን ተግባራት ለማድረግ ደግሞ የሚኬደው የክብሩ መገለጫ እና የስሙ መገኛ ወደሆኑት የእግዚአብሄር ታቦት እና ቤተ መቅደስ ነው፡፡ የሚነበበው የእሱ ገድል የተጻፈባቸው ቅዱሳት መጻህፍት ብቻ ናቸው፡፡ ሰውም ሆነ ቀኑ አይመሰገኑበትም፡፡ የሰው ዝና አይነገርበትም፡፡ እንዲሁም ሌላ ማንኛውም መንፈሳዊ ትርጉም የሌለው ነገር አይደረግበትም፡፡ ስለዚህ ዛሬም ክርስቲያኖች መንፈሳዊ በአላትን ስናከብር እነዚህን ተግባራት ብቻ ለእግዚአብሄር እና ስለእግዚአብሄር ብቻ በማድረግ መሆን አለበት፡፡ ከእግዚአብሄር ውጭ ለሌላ ነገር ቀንን መለየት ወይም መቀደስ፣ የሌላ ስምን መጥራት እና ማክበር ባእድ አምልኮ ይሆናል፡፡

ሁለተኛው ምሳሌያችን ኢየሱስ ነው፡፡ ኢየሱስ ሰንበትን ያከበረው በሽተኞችን እየፈወሰ እንደሆነ ሁሉ በአል የሚከበረው መንፈሳዊ እና ሌሎች መልካም ስራዎችን በመስራት ነው (ማቴ 12፡10-12)፡፡ ሰብአዊ ተግባራትን ማድረግ፣ ዘመድ መጠየቅ፣ በሽተኞችን መጎብኘት፣ ነፍሳትን ወደጌታ መመለስ፣ ስደተኞችንና ምግብ የሌላቸውን መመገብ እና የመሳሰሉት ለሰው የሚጠቅሙ፣ ሰላምን ፍቅርንና ደህንነትን የሚያጎሉ፣ በመልካም ምሳሌነታቸው የሚነሱና ለሌሎች ለመልካም ነገር መነሳሳትን የሚፈጥሩ ተግባራት በበአል ታቅደው ሊሰሩ ከሚችሉ መልካም ስራዎች መካከል ይገኛሉ (ኢሳ 58)፡፡

ሶስተኛ በአል የደስታ ጊዜ እንደመሆኑ መጠን መብላትን፣ መጠጣትን፣ መልበስን፣ መዝናናትን፣ ወዘተ የመሳሰሉ ስጋን ደስ የሚያሰኙ ነገሮች ማድረጉ የሚጠበቅ ቢሆንም በእነዚህ ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ግን የበአሉን መንፈሳዊነት ይሸፍነዋል፡፡ ወደምድራዊነት ማዘንበልን ያሳብቃል (ሮሜ 15፡17-18)፡፡ ራስን ማስደሰት ከእግዚአብሄር ፈቃድ ውጭ ባይሆንም የበአል አብላጫ ትኩረት ግን ከምግቡና ከመጠጡ ይልቅ ምስጋና በማቅረብና የጽድቅ ስራ በመስራት ላይ እንዲሆን እግዚአብሄር ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች ስጋዊ ነገሮችን ከሚገባቸው በላይ ሳናጋንን ወይም እነሱ ላይ የተለየ ትኩረት ሳንሰጥ በምትኩ የእግዚአብሄርን ከፍተኛነት፣ ሀይለኝነት፣ ገዢነት፣ ቸርነት፣ ሰጪነት፣ ጠባቂነት፣ ረዳትነት፣ አዳኝነት ወዘተ በማሰብ በአላትን ማክበር አለብን፡፡

አራተኛ አለማዊ የሆኑ ወይም ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ልማዶችን ሳንቀላቅል ማክበር አለብን፡፡ አንዳንድ በአላት ስማቸው ክርስቲያናዊ ቢሆንም በጊዜ ብዛት ባህላዊ ነገር እየተጫናቸው ሄደዋል፡፡ የፋሲካ እና የልደት በአላትን ማክበሩ ጥሩ ቢሆን ከምናደርጋቸው ነገሮች መካከል ግን ብዙዎቹ መጽሀፍ ቅዱሳዊ መሰረት የላቸውም፡፡ እንዲሁም ለጾም ያለን አመለካከት ከመጽሀፍ ቅዱስ ሀሳብ እንደራቀ የምናስተውልበት ተጨማሪ መረጃ ጾም ፍቺን በአል አድርገን ማክበራችን እና "እንኳን ጾም ልጓሙን ፈታልህ" መባባላችን ነው፡፡ ጾም ልጓም ወይም እስራት ሳይሆን የእግዚአብሄርን ፊት ለመፈለግ በፈቃደኝነት የምናደርገው እና ውጤቱም አስደሳች የሆነ መለኮታዊ ተግባር ነው፡፡

**ተፈጸመ**

## *የቤርያ ቁጥር 38 ጥያቄዎች መልሶች (ሚስት)*

1. ሆሴእ (ሆሴ 1፡2-3)
2. ህዝቅኤል (ህዝ 24፡15-27)
3. ሄሮድስ (ማቴ 14፡3)
4. ሰለሞን (1ነገ 11፡1-10)
5. ናባል (1ሳሙ 25)

## *የቤርያ ጥያቄዎች (ጸሀፍት)*

1. ከመዝሙረ ዳዊት ጸሀፍት መካከል ቢያንስ አራቱን ጥቀስ፡፡
2. ይህ ጥቅስ ከየትኛው መጽሀፍ የተወሰደ ነው? *"አንድ የመጽሐፍ ክርታስ ውሰድ፥ ለአንተም ከተናገርሁበት ቀን ከኢዮስያስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በእስራኤልና በይሁዳ ላይ በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተናገርሁህን ቃል ሁሉ ጻፍበት።"*
3. ያሻር ማነው?
4. ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዲያነብ የተሰጠው መጽሀፍ የማነው?
5. ክርስቲያኖች ጳውሎስ የጻፈላቸውን ደብዳቤዎች እያጣመሙ ከሚተረጉሙ አሳቾች እንዲጠነቀቁ ያሳሰበ ሌላ ጸሀፊ ማነው?